የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ — ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

1st Year No. 5
ADDIS ABABA - 24th August, 1995


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፭/፲፱፻፹፯ ዓ.ም.
የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ...................................................... ገጽ ፶፰


## CONTENTS


Proclamation No. 5/1995
Federal Government Revenues Board Establishment Proclamation ................................................ Page 58.


## አዋጅ ቁጥር ፭/፲፱፻፹፯

## የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የመንግሥት ገቢዎች ቦርድን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭/፲፱፻፹፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪· መቋቋም

፩· የመንግሥት ገቢዎች ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ቦርዱ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል።

### ፫· የቦርዱ ዓላማ

የቦርዱ ዓላማ የመንግሥት ገቢዎች ሥርዓት ባለውና በተቀላጠፈ መንገድ በወቅቱ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና አሰባሰቡንም በበላይነት መምራት ይሆናል።

## PROCLAMATION NO. 5/1995

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE REVENUES BOARD OF THE FEDERAL GOVERNMENT

WHEREAS, it is found necessary to establish the Government Revenues Board;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### *1. Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Federal Government Revenues Board Establishment Proclamation No. 5/1995."

### *2. Establishment*

1. The Government Revenues Board (hereinafter referred to as the "Board") is hereby established as an autonomous organ of the Federal Government.
2. The Board shall be accountable to the Council of Ministers.

### *3. Objective*

The objective of the Board shall be to facilitate conditions for the systematic, efficient and timely collection of Government revenues and to direct their collection.

**፬· የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· የመንግሥት ገቢዎችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማሰባሰብ የሚያስችሉ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓቶች ይዘረጋል ፤ አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል ፤

፪· የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣንን ፤ የጉምሩክ ባለሥልጣንንና የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን በበላይነት ይመራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

፫· አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመንግሥት ገቢ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥትና የክልል የጋራ ገቢ በሚገባ መወሰኑን፣ መሰብሰቡን፣ ሂሳቡም በሚገባ መያዙን ያረጋግጣል ፤

፬· ሥራውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

**፭· የቦርዱ አባላት**

ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

፩· በመንግሥት የሚሾም ባለሥልጣን ................ ሰብሳቢ
፪· የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር .............. አባል
፫· የገንዘብ ሚኒስትር .......................................... ”
፬· የጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ........... ”
፭· የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ . ”
፮· በመንግሥት የሚሰየሙ ሌሎች አባላት ................ ”

**፮· የቦርዱ ጽሕፈት ቤት**

፩· ቦርዱ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል።
፪· የቦርዱ ሰብሳቢ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ይሆናል።
፫· ጽሕፈት ቤቱ፣
ሀ) የቦርዱን ውሣኔዎች ያስፈጽማል፣
ለ) በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የራሱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣
ሐ) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

**፯· በጀት**

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

**፰· የሂሳብ መዛግብት**

፩· ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪· የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

**፱· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

*4. Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1. to set up systems of supervision and follow up aimed at the efficient collection of Government revenues;
2. to direct and supervise the Inland Revenue Authority, the Customs Authority and the National Lottery Administration;
3. to ensure the due assessment, collection and proper keeping of accounts of Government revenues as well as of joint revenues of the Federal and Regional Governments, in accordance with the relevant law;
4. to perform such other duties as help enhance the carrying out of its activities.

*5. Members of the Board*

The Board shall have the following members:

1. an Official to be appointed by the Government .............................................. Chairman
2. the Minister of Economic Development and Cooperation ...................... Member
3. the Minister of Finance ................................ ”
4. the General Manager of the Customs Authority ....................................... ”
5. the General Manager of the Inland Revenue Authority ............................ ”
6. other Members to be designated by the Government ..................................... ”

*6. Secretariat of the Board*

1. The Board shall have its own Secretariat.
2. The Chairman of the Board shall be the Head of the Secretariat.
3. The Secretariat shall:
   a) execute the decisions of the Board;
   b) employ and administer its personnel in accordance with the Federal civil service laws;
   c) own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name.

*7. Budget*

The budget of the Secretariat shall be allocated by the Government.

*8. Books of Accounts*

1. The Secretariat shall keep complete and accurate books of accounts.
2. The Secretariat's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

*9. Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of August, 1995.

Done at Addis Ababa, this 24th day of August, 1995.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE